# እውን ኦርጋን የመዝሙር መሣሪያ ነውን?

ሰሞኑን ሰርገው በገቡ መናፍቃንና በመናፍቃን በተሟኩ በተሟዙ ግለሰቦች ሳቢያ "ኦርጋንን የመዝሙር መሣሪያችን እናደርጋለን! የለም አታደርጉም!" ሳቢያ በቤተክርስቲያን የተጧጧፈ ግብ ግብ እንደነበረ ዓይታቹሀል ሰምታቹሀል አንብባቹሀል፡፡ ለንትርክ ግብግቡ ኦርጋን ምክንያት ሆነ እንጅ ዋናው ችግር ወይም መንስኤው እሱ አይደለም፡፡

የዚህ ችግር መንስኤ ኦርጋን የመዝሙር መሣሪያችን ሚሆን አለበት የሚሉ ወገኖች ሕይዎት ከመንፈሳዊነት ሚራቁ ሥጋዊ ፈቃድ በእነሱ ላይ መሠልጠኑ መንገሡ ነው ኦርጋን የመዝሙር መሣሪያ ሚሆን አለበት እንዲሉ ያደረጋቸው፡፡ ሌላ ምንም እንዳይመስላቹህ ምንፍቅናው የችግሩ ወጡቱ እንጅ መንስኤ አይደለም፡፡

እነኝህ ወገኖች የያዙት ሥልጣን መንፈሳዊ እንዲሆኑ የሚጠበቅባቸው ሆኖ እያለ ሕይወታቸው ከመንፈሳዊነት ሰርቅ አሁን እያሳዩዋቸው ላሏቸው ዘርፈ ብዙ ችግሮች ሊጋለጡ ችለዋል፡፡ እዚህ ላይ አንድ ግልጽ ሚድረግ የምፈልገው ነገር አለ ብዙ ጊዜ "መንፈሳዊ" የሚለውን ቃል ያላአግባብ ያለቦታው ስንጠቀምበት እንስተዋላለን፡፡ መንፈሳዊ ወይም መንፈሳዊያን የሚባሉት የሥጋ ፈቃድ የጠፉላቸው ወይም በእሱ ላይ መሠልጠን የቻሉ፣ ሙሉ ሕይዎታቸው ተግባር አገልግሎታቸው በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩና የተቃኘላቸው ሰዎች ማለትም እራሳቸውን ከዓለም ለይተው በያሉበት፣ በየገዳሙ፣ በየዋሻው፣ በየፍርኩታው፣ በየበረሀው ጠጠ ልሰው፣ ድንዳይ ተንተርሰው፣ ግርምአ ሌሊቱን ፀብአ አጋንንቱን ታግሰው፣ በጾም በጸሎት በሥግደት ተወስነው የተለያዩ ትሩፋት እየፈጸሙ ስለ ስሙ ስለ ክብሩ፣ ለእሱ ስለመገዛት፣ እሱን ስለ ማግኘል፣ ስለማክበር መከራ እየተቀበሉ እየተጋደሉ ሥጋን ከክፉ ሚሻቱና ምኞቱ ጋር የሰቀሉት ቅዱሳንና ቅዱሳት እናት አባቶቻችን ናቸው መንፈሳዊ መንፈሳዊት መንፈሳውያን መንፈሳውያት የሚባሉት እንጅ የላመ የጣመ እየጎሰጎሰ፣ የሞቀ የደመቀ እየለበሰ፣ ሰውነቱን አለስልሶ ቦርጩን አንደፍጦ ተድላ ደስታውን እየኮመኮመ የሚኖረው መነኩሴም ይባል ጳጳስ፣ መምሕርም ይባል ዲያቆን፣ ምእመንም ይሁን ምን እነኝህ ሁሉ መንፈሳዊ አይደለንም" መንፈሳዊነት በከባባድ ተጋድሎ የሚገኝ ጸጋ ሆኖ በሕይወት የሚገለጥ የሚታይ ማንነት እንጅ ተድላ ደስታ እየተኮመኮሙ በምቾት እየተኖረ፣ እያላገጥን እንደተፈለገ የምንሠየመው ስም አይደለም፡፡

ቤተክርስቲያን ልጆቿ ይኖሩበት ዘንድ የሠራችው ሁለት ዓይነት ሥርዓት አላት፡፡ በምናና እና በዓለም የምንኖርበት፡፡ በዓለም ሥርዓት ለምንኖር (ልብ በሉ በዓለማዊ ሥርዓት አላልኩም) በዓለም ሥርዓት ለምንኖር ክርስቲያኖች የተፈቀደው በምናና ሥርዓት ለሚኖሩት ፈጽሞ ክልክል ነው፡፡ በዓለም ለምንኖረው የሚያስኮንነው በምናና ለሚኖሩት መቀላለፍ ነው፡፡

ለምሳሌ አግብቶ መውለድ፣ ከምግብ ጥሉላትን መመገብ የመሳሰሉት፡፡ መንፈሳዊያን የሚባሉት መናኞቹ ናቸው፡፡ እኛ በከተማ በዓለም ሥርዓት የምንኖረው ግን ከእኛ መሀል ሆነው በመናኝ ሥርዓት ከሚኖሩት ከወስጣቸው ማቅ ለብሰው ከላይ ግን ሰፋቸውን ግጥም አድርገው ሳይታወቁ ከሚኖሩት ሳያጡ ቆሎ ወይም ሌላ መናኛ ምግብ በጥቂቱ እየተመገቡ ሲሰግዱ ከሚያድሩት በየመሥሪያ ቤቱ ካሉት እብድ የኔ ቢጤ መስለው በየጎዳናው ከሚኖሩት ሥውር ባሕታውያን በስተቀረ መንፈሳዊያን አይደለንም፡፡ ዓለማዊያን ነን እያልኩም አይደለም፡፡ ቤተክርስቲያን የሠራችልንን የዓለም ሥርዓት ጠበቀን ከኖርን መንግስቱን ለመውረስ የምንበቃ ክርስቲያኖች እንባላለን እንጅ መንፈሳዊያን አይደለንም አንባልምም፡፡

ከዚህ ውጭ ግን በክርስቲያናዊ ሕይዎት ወስጥ አክራሪ ለዘብተኛ የሚባል ክፍፍል ወይም የሕይዎት ዘርፍ የለም፡፡ ሁሉም ክርስቲያን አምላካዊ ሕጉን ሥርዓቱን የማጠበቅ ግዴታ አለበትና፡፡ ሕግና ሥርዓቱን

የሚጠበቅና ያለሚጠበቅ ጉዳይ በእኛ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ለማንኛወም ክርስቲያን ግዴታ ነው፡፡ ክርስቲያኖች ነን እስካልንና መዳንን እስከፈለግን ጊዜ ድረስ ከቸርነቱ ጋር የግድ በዚህ ክርስቲያናዊ ሕይዎት የሚከፍ የሚጠበቅ የመኖር ግዴታ አለብን፡፡ በሚሆኑም አክራሪ ለዘብተኛ የሚባል ፍረጃ በቤተክርስቲያን ቦታ የለወን አይታወቅምም፡፡

ወደ ቀደመው ነገራችን እንመለስና እናም እኛ ሰዎች ሥጋዊ ፈቃድ በወስጣችን ሲሠለጥንብን ሲነግሥብን ይሄንን ክፉ ሥጋዊ ፈቃዳችን ፍላጎታችን ለሚርካት ቤተክርስቲያን ከፈቀደችልን ሕይዎት የሚጼረር የተለያየ ተግባርን ለሚፈጸም እንንገደዳለን፡፡ ከዚህ ስብራታችን እራሳችንን ጠየነን የማኅት አቅምና ፍላጎት የለንምና ያኔ መወደቃችንን ድል ማሳታችንን ላለማማን የወደቅንበትን ጉዳይ የጽድቅ ሚልክ ለማስያዝ እንሯሯጣለን፡፡ እየሆነ ያለው ይሄው ነው ሌላ አይደለም፡፡

በዚህ ሐደት ነው የመናፍቃን ድርጅቶች ሊፈጠሩ የቻሉት፡፡ በዚህ ሂደት ነው ቃሉ እንደሚለው ኃይማኖት አንድ ሆና እያለች ኤፌ. 4፤5, ይሁ. 1፤3, ዕብ. 3፤14, ኤር. 6፤16 በሃይማት ስም እንደ ማኅግሥታቱ ድርጅት ሚጃ በመቶ ሽዎች የሚቆጠሩ ሃይማኖት ማስል ድርጅቶች እንደ አሸን ሊፈሉ የቻሉት፡፡

በዚህ ምክንያት ነው ቀድሞ የእኛ ወገን የነበሩ ዛሬ ላይ ግን በመናፍቃን ጉረኖ፣ በእስላም ጋጣ፣ በአረሚዊነት ጉድጓድ ታጉረው የምናገኛቸው፡፡ ማንም ሰው እውነትና ሃይማኖት የት እንዳለና ማን እንደሆነ ጠፍቶት እንዳይመስላቹህ የተለያየ ጎሬ ወስጥ ተወሽቆ የምታዩት፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ከደካማነቱ ከሥጋዊ ምኞቱና ፍላጎቱ የተነሣ ላለበት የተለያየ ዓይነት ክፉ ሥጋዊ ፍላጎትና ፈቃድ ማሸሸጊያ ጫካብል ይሠራና እየሐደ ይታጎራል እንጅ እውነት የእግዚአብሐር ፈቃድና ሃይማኖት ማንና የትኛው እንደሆነ ማንንም ይጠፋዋል ብየ አላምንም፡ ማንም ወንጌል ባይሰበክለትም እንኳ እውነትና የእግዚአብሐር ፈቃድ የት እንዳለ ከነጻ ኅሊናው ፍርድ ሚዳቱ የሚቀር ነው፡፡ ነገር ግን ይሄንን የነጻ ኅሊናወን ፍርድና ምክር እንዳይሰማ ሥጋዊ ጥቅመኛ ፍላጎቱ ስለሚከለክለው ስለሚያደነቁረው ነው በያለበት የያዘወን እውነት እያስመሰለ እራሱን በሚታለል የሚኖረው፡፡

ወደ መናፍቃን ጉረኖ እየሐዱ የሚታጎሩት መናፍቅ የሆኑት መጾም፣ መጸለይ፣ ማስገድ፣ ስለሚይወዱ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን በኃጢኣት እንዳጨማለቁ ሰዎችን ኃጢኣት ለማሠራት ነጻነት ለማስጠት የመጣ ይመስል የሃይማኖትን ግብና ዓላማ እጅግ በሚዘረር ሚልኩ "በኢየሱስ አምነናልና የፈለገንን ያህል መተላለፍ ብንፈጽም (ኃጢኣት ብንሠራ) አንዴ በጸጋው ድነናልና በምንፈጽመው መተላለፍ አንጠየቅም ኢየሱስ ዕዳችንን ከፍሎልናል" በማለት እራሳቸወን እያታለሉ ሚድረግ የሚፈልጉትን ሁሉ ያለመሳቀቅ ለሚድረግ ሲሉ የሐዱ ናቸው፡፡

ወደ እስላሙ እየሐደ የሚታጎረው ደግሞ እስከ ሰባት ሚስት በማግባት ያለበትን የሴሰኝነት ጥማት ለሚርካት፣ ጾም ሥጋን ሚድከም ሥጋን በሚድከምም ሰወነትን ከሥጋዊ ፈቃድና ምኞት ፍላጎት በሚራቅ ለአምላክ ማስገዛት ማለት ሆኖ ሳለ፤ ጾም በሚሉት ሰዓት "ይሄ የጾም ነው ይሔ ደግሞ የግድፍት ወይም የፍስክ ነው" ተብለው ሳይከለከሉ ጮማወን መቁረጥ፣ እርጎወን መጋት፣ ቅቤወን መዋጥ፣ እንቁላሉን ማስልቀጥ ባጠቃላይ ጥሉላትን (የእንስሳት ተዋጽኦን) እንደፈለጉ ለመጥረግ ለሚከተት፣ ሚስቶቹን እንደ እንስሳ ለመግዛት ሲደብሩትና ፈትቶ ሌላ ማግባት ሲፈልግም ባዶ እጃቸወን ለማኘት ወዘተረፈ. ሲል የሐደ ነው፡፡

እግዚአብሐርን ከማመን ወደ አለማመን ወይም ወደ አረሚዊነት ጎራ እየሐደ የሚወሸቀው ወገናችን ደግሞ የሰው ልጅ ሆኖ ከእናቱ፣ ከመቅደሱ፣ ከሚደሪያው ከቅድስት ድንግል ሚርያም በስተቀር ያልበደለና የሚይበድል፣ ኃጢኣት ያልሠራና የሚይሠራ አለመኖሩን ባለሚዳት በኃጢኣት ሲወደቅም በንስሐ ማኅት፣

ከእርኩስነት ወደ ቅዱስነት ማለወጥ እንደሚቻል ባለማንዘብ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ኃጢአት ይሠሩና ያ የሠሩት ነገር ኃጢአት እንደሆነና እንደሚያስኮንን ሲያወቁ "ከዚህ በኋላ እረክሻለሁና ከእንግዲህ እግዚአብሔር በንጹሕ ሰው ዓይን ላያየኝ ነገር ምን አደከመኝ!" በሚል ቀቢጸ ተስፋ ፈላስፋ ለማሳል በማማከር እራሳቸውን በማታለል እግዚአብሔርን ከማመን ወደ አለማመን ወይም አረማዊነት ይለወጣሉ፡፡ የእነኝህ ሰዎች ምክንያት ይሄ ብቻ አይደለም፡ ኃጢአት ነወና አታድርጉ ማባሉ ሳይመቻቸው ሲቀር እንደፈለጉ ለመሆንም እግዚአብሔርን ከማመን ወደ አለማመን ይለወጣሉ፡፡

እናም እንግዲህ የዚህ የርእሰ ጉዳያችን ችግር መንስኤ ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ ሰው በአንድ ሐሳብ የሚይስማማበት ብዙ እወነት ያለ ይመስል ሥጋዊ ምኞቱንና ፍላጎቱን ለማስተናገድ አመቻችቶ የፈጠረወንና የያዘወን የየራሱን መንገድ እወነት እያስመሰለ እራሱን የሚሸነግልበት ምክንያት ለግላዊ የሥጋ ምኞቱ ፍላጎቱ መሻቱ መሸነፉና ሽንፈቱን ለመሸፈን የሚያደርገው ጥረት ነው ከአንዲቷና ለሥጋው ካልተመቸችው ከእወነተኛዋ መንገድ እየወጣ በየራሱ ጉረኖ የሚወሸቀው እንጅ ሌላ አይደለም፡ "በጠበበውደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደውደጅ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነወና ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤ ወደ ሕይወት የሚወስደውደጅ የጠበበ መንገዱምየቀጠነ ነወና የሚያገኙትምጥቂቶች ናቸው" ማቴ. 7፤13-14

ወደ ርእሰ ጉዳያችን ስንመለስ ቤተክርስቲያን ልጆቿ ይኖሩበት ዘንድ ለሁሉም ነገር ሥርዓት ሕግ ደንብ ወግ ባሕል ይትበሀል አላት፡፡ እንደፈለግን የፈለግነወን ከየትም አምጥተን እንድናጉርባት እንድንጫንባት የሚያስችል ክፍተት የላትም፡ አጥር ገደብ ልክ የሌላት እንደተፈለገ የሚዘለልባት የሚጨፈርባት ልቅና ሜዳ አይደለችም፡ በሯ ጠባብ መንገዷ ቀጭን የሚገቡባትም ጥቂቶች ናቸው እንዳለው ክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌሉ፡፡

ሐዋርያት በሚልእክታቸው "ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን" 1ኛ ቆሮ. 14፤40 እንዳሉ ሁሉ ቤተክርስቲያን ለሁሉም ነገሯ አገባብና ሥርዓት የሠራች ስንዱ እመቤት ናት፡፡ ይህ አገባብና ሥርዓት ያልተመቸው የጠበበው ካለ የሚቻለወና መብቱ የሆነው ነገር ቢኖር ጥሎ መውጣት ነው እንጅ ቅጽር ማፍረስ ሜዳ ሥርዓት አገባብ መሻር አይደለም፡ ይሄ ፈጽሞ አይፈቀደም!!

ሁሉም ነገር ዓለማዊ አለው መንፈሳዊም አለው፡ ሥጋዊ አለው ነፍሳዊ አለው፡ በዚህም መሠረት ቤተክርስቲያን ለአዘማመር ወይም ለአዚያዚያም ብቻ አይደለም ለአበላል፣ ለአጠጣጥ፣ ለአረማመድ፣ ለአነጋገር፣ ለአለባበስ፣ ለወዘተረፈ. ለሁሉም ነገር ክርስቲያናዊ የሆነ ሥርዓት አላት፡፡ ክርስቲያናዊ አግባብነቱን እንዳይለቅም ሁሉም ገደብና ልክ አለው፡ ከልኩ ከገደቡ እንዲያልፍ አይፈቀደም አይፈለግም፡

ቤተክርስቲያን በሥርዓቷ የተፈቀደ ቢሆንም ይህ የተፈቀደው ነገር ልኩን ገደቡን እንዲያልፍ የምትፈቅደው ምንም ነገር የላትም፡ የማልገያ እቃም ዓለማዊ አለው መንፈሳዊም አለው፡ ልዑል እግዚአብሔር በዓለማዊ ዕቃዎች አይከብርም አይገለገልም አይማስገንም፡ ለምሳሌ በዘማ ልብስ አይቀደስም ሌሎች አገልግሎቶች አይሰጥም፡ እንኳንና ሊቀደስ ሊገለገልበት ቀርቶ በሌሎች ቦታዎችም እንኳን ክርስቲያኖች እንዲጠቀሙበት ፈጽሞ አይፈቀደም፡

ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚሆኑ እቃዎችና ንዋየ ቅድሳት የራሳቸው ማለያ አላቸው፡ ለዓለማዊ አገልግሎት የተባሉት ዕቃዎች ደግሞ የራሳቸው ማለያ አላቸው፡ የዓለማዊዎቹ ሥጋዊ ስሜትን የሚቀሰቅሱ፣ የሚያጎሹ፣ የሚነጡ ናቸው፡ የመንፈሳዊዎቹ የሚያረጋጉ፣ የሚያሰክኑ፣ የሚገሩ፣ ስሜት እንዳይገነፍል እንዳይጎሽ የሚያቅቡ፣ የሚሰበስቡ፣ የሚማስጡ ናቸው፡

በዚህም መሠረት የመዝሙር መሣሪያዎቿ ከልኩና ከሚፈለገው ከገደቡ በላይ እንዳይሆኑ የተደረጉ ልክና ገደብ ያላቸው በመሆናቸው የተመረጡ ናቸው፡፡ የዓለማዊ የዜማ መሣሪያዎች ሥጋዊ ስሜት ለመቀስቀስ፣ ለማናጥ፣ ለማስጎሸት፣ ለማክበድ፣ ለማክከር፣ አቅል ለማሳት የችሎታቸውን የመጨረሻ ጥግ ድረስ ሔደው ለሥጋዊ ተግባር አስፈላጊውን ወጡት እንዲያስገኙ እንዲያመጡ ተደርገው የተሠሩ ናቸው፡፡ እነዚህ መሣሪያዎች ሁሉም ሊባሉ በሚቻል ደረጃ የተሠሩት ዓለም ህልዎተ እግዚአብሔርን በካደበት፣ ሃይማኖት በተናቀ በተዋረደበት፣ ክህደት በሠለጠነበት፣ ሥጋዊና የጥፋት ሥራ ልክ ባጣበትና ቁምነገር ተደርጎ በተቆጠረበት በቅርቡ ዘመን ነው፡፡

በእርግጥ ለእነዚህ የዜማ መሣሪያዎች መሠራት በሠረታቸው አስቀድመው የነበሩት የትንፋሽ፣ የክር ወይም የጅማት፣ የምት መሣሪያዎች ናቸው፡፡ ይሁንና ዓላማቸው ሥጋዊ ሥሜትን ከላይ በጠቀስኩት መልኩ መቀስቀስ ማናጥ ማጉወጥ ስለሆነ ሁሉም ልክና ገደብን የተላለፉ ናቸው፡፡ በመሆኑም ብንጠቀማቸው ያልተፈለገ ወጤት ስለሚያስከትሉ እነኝህን መሣሪያዎች ለመንፈሳዊ አገልግሎት ማጠቀም አይቻልም የተከለከለ ነው፡፡ የመንፈሳዊነት አንዱና ማለያ ጠባዩ ገደብና ልክ ነው፡፡ የዓለማዊነት ደግሞ ገደብና ልክ አልባነት ሥጋዊ ጥቅምን አሳዳጅነት ነው፡፡

ይሄንን ስል ባጠቃላይ የኪነብጅታ (የቴክኖሎጂ) ወጤት የሆኑ እቃዎች የረከሱና ለቤተክርስቲያን አግልግሎት የማይገቡ ናቸው ማለቴ እንዳልሆነ ባለ አእምሮ ሁሉ የሚረዳኝ ይመስለኛ፡፡ ለምሳሌ የድምፅ ማጉያን እንጠቀማለን፡፡ እሱን ማጠቀማችን በቤተክርስቲያን ሕግ ደንብ ሥርዓት ቀኖና ካስፈለገም ዶግማ ላይ የሚያመጣው ለወጥ ተጽእኖና ጉዳት ስለሌለ፡፡

እንግዲህ ችግሩ የሚፈጠረው ችግሩን የሚፈጥሩት ሰዎች ይሄ ገደብ ሥርዓትና ደንብ የሚጠብቸው ሥጋዊ ስሜት ፍላጎትና ፈቃድ የገነነባቸው የሰረጸባቸው የነገሠባቸው ሰዎች ገደቡ ልኩ ይሄንን ፍላጎታቸውን ለማሟላት ስለማይፈቅድላቸው እሱን ለማሟላት ገደቡን አጥሩን ልኩን መጣስ ሥርዓትና ደንቡን ማፍረስ ሲፈልጉና ሙከራ በሚያደርጉበት ጊዜ ነው፡፡

እርግጥ ነው እንደ ልበ አምላክ ዳዊትና የእስራኤል ጎበዛዝት እንደ የጥምቀት በዓል ኮበሌዎችና ቆነጃጅት ወይዛዝርትና እናቶች በዘፈን በዳንኪራና በጭፈራም እግዚአብሔርን ማመስገን ይቻላል፡፡ ይቻላል ሲባል ግን ዘማዊያን ወሲባዊ ስሜትን ለመቀስቀስ መቀመጫና ሌላ የሰውነት ክፍልን በአጉል ሁኔታ እያወዛወዙ በሚያደርጉት የዳንኪራና የጭፈራ ዓይነት እግዚአብሔርን ማመስገን ማክበር ማገልገል ይቻላል ማለት እንዳልሆነ ማንም ሊረዳው የሚችለው ነገር ይመስለኛል፡፡ አዚያዚያም አጨፋፈራችን ግብረገባዊ የሆነ እንጅ ልቅና ሥርዓት አልባ ጩኸትና ሁከት ያለበት አይደለም፡፡ ይህ የሚያሳየው ጭፈራውና ዳንኪራውም ራሱ ገደብና ሥርዓት ልክ የሌለው ልቅ አለመሆኑን ነው፡፡

ወደ ኦርጋኑ ጉዳይ ስንመጣ እነዚህ ወገኖች ኦርጋንን በእግዚአብሔር ቤት አስገብተው በመጨረሻ ሥጋዊ ስሜታቸውን ለማርካት ኦርጋን ሃይማኖታዊ ተቀባይነት እንዲኖረው የሔዱበትን ጥግ ሳይ በእውነት ነው የምላቹህ በእጅጉ ነው የደነቀኝ የገረመኝም፡፡ ለነገሩ ሰይጣን ለማሳሳት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ከመጥቀስ ጀምሮ የብርሃንን መልአክ እስከመምሰል ድረስ እራሱን ይለውጣልና አገልጋዮቹም የጽድቅ አገልጋዮች እስከመምሰሉ ድረስ እራሳቸውን ይለውጣሉና የጥፋት ሥራውን ለመሥራት ለማሳት ከዚህም በላይ ይበረታልና ይጠበባልና ይህ ድርጊታቸው ሊገርመኝ ባልተገባ ነበር፡፡

ዳንኪረኞቹ ዋቢ እያደረጉ እንደሚጠቅሷቸው የቤተክርስቲያን አባቶች እንደ ቅዱስ ያሬድና ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የቃላት አጠቃቀም አርጋኖን ማለት ምስጋና ማለት መሆኑ ግልጽ ሆኖ ሳለ የቃላቱ መመሳሰል ተመቸን ብለው አርጋኖን የተባለው ኦርጋን ነው በማለት ድርቅ ብለዋል፡፡

መዝገበ ቃላቶቻችንን ያዘጋጁ ሊቃውንት እነ አለቃ ኪዳነ ወልድክፍሌ፣ ከሳቴ ብርሃን ተሰማ ሀብተ ሚካኤል፣ ደስታ ተክለ ወልድ፣ ሊቀ ኅሩያን በላይ መኮንን አርጋኖን ለሚለው ቃል ትርጉም ሲሰጡ በምእራባዊያኑ መዝገበ ቃላቶች ጥንታዊ ኦርጋን ተብለው የተገለጹትን መሣሪያዎች በማስቀመጥ አርጋኖን ማለት ኦርጋን ማለት እንደሆነ በማለጥ ይሄንን ስሕተት ደግመውታል፡፡ በእርግጥ የጸሎት መጽሐፍ ማለት እንደሆነም በሁለተኛ ትርጉምነት አስቀምጠዋል፡፡ ይሁንና ግን አርጋኖን ለሚሉት የዜማ መሣሪያ ተመሳሳይ ትርጉም ሊሰጡ አልቻሉም፡፡ አንደኛው ዐሥር ቀዳዳ ያለው ዋሽንት መሰል መሣሪያ ሲያደርገው ሌላኛው እንደበገና ያለ ባለ አውታር ያደርገዋል፤ ሌላው አኮርዲዮን የሚመስልን ሥዕል ሲያሳይ እንደገና ሌላው ደግሞ ሰባት ዋሽንት መሰል መሣሪያዎች ተደራርበው ያሉበትን የትንፋሽ መሣሪያ ያሳያል ብቻ የተለያየ ነው ተመሳሳይ አይደለም፡፡ ምናልባት ኦርጋን እንደ የጥቅል የዜማ መሣሪያ ማጠሪያ ተደርጎ ይገለጽ ስለነበረ ስሕተቱ ከዚህ በማጨየተፈጠረ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ችግር በእኛ መዝገበ ቃላቶች ላይ ብቻ ያለ ችግር ሳይሆን በምዕራባዊያኑም ላይ ያለ ችግርም ነው፡፡

የሆነ ሆኖ አርጋኖን ማለት ኦርጋን ማለት ነው ብለው ከደረቁ ይህ መሣሪያ ከላይ የመዝገበ ቃላት ጸሐፊዎች ከጠቀሷቸው የዜማ መሣሪያዎች አንደኛው ማለት ነው እንጅ አሁን እነሱ እየተጠቀሙበት ያለውን ኦርጋን ማለት እንዳልሆነ ልንግባባ የምንችል የሚባባንም ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ዋሽንት ወይም በገና በሚመስል የዜማ መሣሪያና አሁን ባለው ኦርጋን መካከል በግልጽና በየትኛውም የአእምሮ ብስለት ደረጃ ያለ ሰው ሁሉ በቀላሉ ሊረዳው የሚችለው ሰፊ ልዩነትና ርቀት አለና፡፡ ስለዚህ ስም ስለተመሳሰለ ብቻ አንድ ናቸው ልንል አንችልም ማለት ነው፡፡

ዳንኪረኞቹ አሁን እየተጠቀሙበት እየተገለገሉበት ያለው ኦርጋን የአሁን የቅርብ ጊዜ የኪነብጀታ (የቴክኖሎጂ) ውጤት የዜማ መሣሪያ ከ1934 ዓ.ም. ጀምሮ የመጣ መሆኑ እየታወቀ በእነ ቅዱስ ያሬድና በቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ዘመን የነበረ የዜማ መሣሪያ አስመስሎ "ኦርጋን ማለት አርጋኖን ነው" በማለት "ቅዱስ ያሬድና ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በድርሰቶቻቸው ደጋግመው በማወደስ ያነሡት የዜማ መሣሪያ ነው! በቀድሞ ዘመንም በቤተክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት ይሰጥ ነበር" በማለት ተቀባይነት አግኝቶ የቤተክርስቲያን አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ለሚታለል ማጭበር ይሄንን የሚሉት ሰዎች ስሜታቸውንና ከደካማ ሥጋዊ ፈቃድ ፍላጎታቸው የመነጨውን ግላዊ ፍላጎታቸውን ሃይማኖታዊ ሚልክ በማስያዝ የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚሠሩ ሚሊቲዎችና ከንቱ ግብዞች መሆናቸውን ያጋልጥ ያረጋግጥ ካልሆነ በስተቀር እውነትን የሚያሳይ የሚያረጋግጥ አንዳችም ነገር የለውም፡፡

"አርጋኖን ወይም ኦርጋን የሚለው ስም ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ ስለነበረ አሁን ኦርጋን የሚባለውን የዜማ መሣሪያ ማጠቀም አለብን!" ብሎ ማለት ልብስ አስቀድሞ የነበረ እንደመሆኑና በኋላ ላይ ግን የተለያየ ቅርጽ ይዘትና ጌጥ እየወጣለት እየተደረገበት እግዚአብሔር የሚጠላው ሰውን የሚያሳስት የሚያሰናክል የዘማ ልብስ እንደማማጣቱና ይህ ልብስ ልብስ የሚለውን የቀድሞውን ስም አሁንም ስለያዘ ብቻ ይሄንን የዘማ ልብስ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት እንጠቀምበታለብ ብሎ እንደማለት ነው፡፡

ይሄ ደግሞ እጅግ የተሳሳተና የሚያስቀስፍ ለመሆኑ የፈለገውን ያህል ቢስቱ እነኝህ "ወንጌል የገባን የወንጌል አገልጋዮች ነን!" የሚሉትም የሚጠፉቸው አይመስለኝም፡፡ ከዓለማዊ የዜማ መሣሪያዎች እንደ ኦርጋን ሥጋዊ ስሜትን በከፍተኛ ደረጃ የሚነጥ፣ የሚቀሰቅስ፣ የሚኮርቅ፣ የሚያረካ የዜማ መሣሪያ

የለም፡፡ ከልብስ የዘማ ልብስ እንዳለ ሁሉ ከዜማ መሣሪያም ኦርጋን የዘማውያን የዜማ መሣሪያ ነው፡፡ እንደ በገናና ሌሎች የመዝሙር መሣሪያዎቻችን ስክነትን፣ ነፍሳዊ ተመስጦን፣ ሰቂለን፣ አንቃዕዶን፣ እርጋታን፣ ሥነ ሥርዓትን የሚያስይዝ የሚያስደምም መሣሪያ አይደለም፡፡ ከላይ በገለጽኩላቹሁ ማለኪያ መሠረት ለመግልገያ ዕቃዎችና መሣሪያዎችም ዓለማዊ ወይም ሥጋዊ እና መንፈሳዊ ወይም ለሰማያዊ አገልግሎት የተመቹ መሣሪያዎች አሉ ብለናልና ይህ ኦርጋን የተባለው የዜማ መሣሪያ ዓለማዊና ሥጋዊ ነው፡፡ ለሰማያዊ አገልግሎት የሚሆንና የተገባ የተመቸ አይደለም፡፡

እነዚህ ደኩማን የሚፈልጉት ከቅዳሴ እስከ ማሕሌት ከኪዳን እስከ ሰዓታት ሌሎቹንም ሰማያዊ የዜማ ሀብታችንን በኦርጋን ጩኸት ሰማያዊ ቃናና ለዛቸው ድራሹ እንዲጠፉ ወሎ አድሮም የዜማ ምልክቱ እንዲጠፉ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ሀብታችን ለቀኑብንና እሴቶቻችንን በተለያየ ዘዴ ለማጥፋት ከቀድሞ ጀምሮ ብዙ ለሚጥሩብን ባዕዳን ቅጥረኞች ናቸው፡፡ ኦርጋን ገባ ማለት ሳክስፎን፣ ጊታር፣ ጃዝ (ድራም) እና ሌሎቹም የዘፈን መሣሪያዎች ገቡ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ኦርጋን እነዚህን መሣሪያዎች ሁሉ በውስጡ የያዘ የዘፈን መሣሪያ ነውና፡፡

ለዚህም ነው እነዚህ ዳንኪረኞች ቀደምት አባቶቻችን እንኳንና በኦርጋን በቤተክርስቲያን የመዝሙር መሣሪያዎች እንኳ እንዲታጀቡ በፍጹም ያልፈቀዱትን ቅዳሴውንና ሰዓታቱን ሌላውንም የጸሎት አገልግሎት በኦርጋን ጩኸት እያጀቡ ሰማያዊ ጥዑመ ዜማው ጣዕሙ ምልክቱና ቃናው በኦርጋኑ ጩኸት እንዲሸፈን እንዳይደመጥ እንዲታፈን ብሎም እንዲጠፉ እያደረጉ ያሉት፡፡

አስቀድሞም አባቶቻችን ቅዳሴውን ሰዓታቱን ኪዳኑን ምሕላውን ሌሎች የጸሎት አገልግሎቶችን በዜማ መሣሪያ እንዳይታጀቡ የማሕሌቱ ዝማሬ ብቻ በመዝሙር መሣሪያዎች እንዲታጀብ ሥርዓት የሠሩት፡፡ ይሄንን ያደረጉት ምክንያት ስላላቸው እንጅ እንደ ማሕሌቱ ዝማሬ ሁሉ ቅዳሴውም ሰዓታቱም ምሕላውም ኪዳኑም ሌሎች የጸሎት አግልግሎቶች ወይም ሥርዓታትም በመዝሙር መሣሪያዎች መታጀብ የሚገባ ሆኖ ይሄንን መደንገግና ማድረግም አቅቷቸው አልነበረም፡፡ እነዚህ የጸሎት ሥርዓታት **ጸሎት** እንደመሆናቸው ማጠን እያንዳንዷን ሰማያዊ የዜማ ቅንጣት፣ ጣዕም፣ ወዝና ቃና ያለ አንዳች ደባልና ተደራቢ ድምፅና ኳኳታ ወይም መሣሪያ በጥሞናና በተመስጦ መደመጥና መደረግ ያለባቸው በመሆኑ እንጅ እንደማሕሌቱ ዝማሬ ወይም **ምስጋና** እንደምስጋናነቱ በመዝሙር መሣሪያዎች መታጀብ የሚያስፈልጋቸው አይደሉም አይገባምም፡፡

እነ ዳንኪረኞች ግን የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ነን እያሉ ይሄንን ምክንያት ወይም ምሥጢር አያውቁም፡፡ መንፈሳዊነት ስለሌላቸው ይሄ አይገባቸውም፡፡ መረዳት የሚችል ማስተዋልና አቅም ስለሌላቸው ባልገባቸው ነገር ላይ በድፍረት የሚሠሩትን ቅዳሴውን ሰዓታቱንና ሌሎች የቤተክርስቲያንን የጸሎት ሥርዓታትን በኦርጋን በማጀብ እያወኩ ይገኛሉ፡፡ በዚህም ድርጊታቸው ባለማወቅም ቢሆን የቤተክርስቲያንን ሥርዓት ደንብና ሕግ ጥሰዋል አፍርሰዋል፡፡

በማወቅም ብቻ ሳይሆን እንዲህ ዳንኪረኞቹ እያደረጉት እንዳለው ባለማወቅ ሕግ ሥርዓት ደንብ ቀኖና ትውፊት ሊጣስ ሊፈርስ ሊሻር የሚችልበት አጋጣሚ እንዳለ ስለሚታወቅም ነው ቅዱስ ቃሉ በጥቅሉ ሳይገባን ጠቃሚ ትክክል የሠራን ማለሎን የነበረውን ሥርዓት በማፍረስ አዲስ ደባል ነገርን በማምጣት እንዳንሳሳት ጥፋት እንዳንሠራ “የአባቶችን ድንበር አታፍልስ” (ምሳሌ 22፡ 28) ሲል የሚያስጠነቅቀን፡፡

እነኝህ ተኩላት ችግር ጣዖት የሆነባቸው የኦርጋን ፍቅር ብቻ በሆነ ለመፍትሐው ባልቸገረን ነበር፡፡ ብዙ ጣጣ አለ፡፡ እጅግ የሚገርመኝ ነገር ቢኖር በዚህ የመናፍቃን ቡድን ወስጥ ያሉ ግለሰቦች እንዲህ የሥጋዊ ምኞት ፍላጎታቸው ባሮችና ይሄንን ድካም ደዌያቸውን በሌሎች ላይ ለማጋባት ለመጫን የሚጥትኑ ተኩላት

ሆነው እያለ እራሳቸውን ወንጌል የገባቸው እንደሆኑና ለወንጌል አገልግሎት ቀናእያን እንደሆኑ ቆጥረው ይሄንን ሲያስተጋቡ ትንሽም እንኳን ሐፍረት የምትባል ነገር የሚይሰማቸው መሆናቸው ነው፡፡

የእነሱን ጩኸታቸውን ብቻ ለሚሰማ የሚሉት ነገር እውነት ሳይመስለው የሚቀር አይመስለኝም፡፡ ለዚህም ይመስለኛል ጥቂት የሚይባሉ ተከታዮችን ሊያገኙ የቻሉት፡፡ ገለጥ አድርጎ ለተመለከታቸው ግን ለወንጌል ቀናእያን ሊሆኑ ቀርቶ ጩርሶ ወንጌል በተነበበበት ዐወደ ምሕረት እንኳን አልፈው የሚያውቁ አይመስሉም፡፡ ተግባሮቻቸው ነጣቂ ተኩሎች እንጅ ማማህራን ሐዋርያት እንዳልሆኑ ያሳያሉ፡፡

ጌታ በወንጌሉ ተከታዮቹ አሞኞቹ አገልጋዮቹ አነማንና የት ድረስ ምን በሚድረግ እሱን ሊከተሉት ሊያምኑት እንደሚገባ ሲናገር "በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ። እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንምተሸክሞይከተለኝ። ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል። ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?" በማለት በምን ዓይነት ክርስቲያናዊ ሕይዎት ታንጸው መኖር እንዳለባቸው ያስረዳ ሆኖ እያለ ቤተክርስቲያንም ይሄንን ቃለ አምላክ መሠረት አድርጋ መጋቢያየ ላይ እንደገለጽኩት ክርስቲያናዊ ሕይዎትን በሁለት ዘርፍ ከፍላ ክርስቲያናዊ ሕይዎት ምን ማማስል እንደሚገባው የገነገገቻቸውን ሥርዓትና ቀኖና በመቃወም ባለመቀበል ለሥጋዊ ጥቅማቸው በሚድር "ጾም በዝቷል ይቀነስ፣ ቅዳሴው እረዝሟል ኪዳን ከቅዳሴ ማኅል ይወጣ ቅዳሴውን በ15 ደቂቃ ያሳጥረዋል" በማለት እንደ ቅዳሴኑ መሆን ማደል ሲሳናቸው ከሥጋዊነታቸው የተነሣ መንፈሳዊነት ስለሌላቸው ሊቀበሏቸውና ሊረዷቸው ያልቻሏቸውን የቤተክርስቲያን ቅዳሴት መጻሕፍትን "ተረትተረት ናቸው" በማለት፣ በወላዲተ አምላክና በሌሎች ቅዱሳን ላይ የድፍረትና የክህደት ንግግር በመናገርና ሌሎች የክህደት ትምህርት በሚርጩት ስተው እያሳቱ እያሰናከሉ ይገኛሉ፡፡ የቀራቸው ነገር ቢኖር እንደመናፍቃኑ ሁሉ "በጸጋው ድኅሀል የምን ጾም ጸሎት ሥግደት ነው!" ማለቱ ነው፡፡ ይሄንንም ቢሆን በይፋ በአደባባይ አይበሉ እንጅ በየጓዳውማ ያለዚህ ሌላ ምን ስብከት አላቸው፡፡

ኑፋቄያቸውን በከፊል እኒሁ ዕብደት እያንገላታቸው ያሉት አባት ተብየ እርጅና እንኳን ሥጋዊ ምኞትና ፈቃዳቸውን ሊገታላቸው ሊያደክምላቸው ያልቻለላቸው አበኅ ሜልከጸደቅ የተባሉት ሰው በ2011 ዓ.ም. ቶሮንቶ ካናዳ "የቅዳሴያችን ይዘት" በሚል ያሳተሙትን መጽሐፍ በመሚለከት ሚጋገጥ ይቻላል፡፡ እኒህ ሰው በቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን ከዚያም በፊት ከድሮ ጀምሮ ችግር ያለባቸው ሰው ናቸው፡፡ በወቅቱ በእሳቸው ላይ እርምጃ አለመወሰዱ "ከማማህሩ ደቀ መዝሙሩ" እንዲሉ ዛሬ በዙሪያቸው ያሉትንና ለጽጽስና ያበቋቸውን የባሱ ተኩሎች ለሙፍራት ችለው የቤተክርስቲያንን ማንነት፣ እሴት፣ ሥርዓት፣ ዶግሙ ቀኖና እንደፈለጉ ለማለባበጥ ለማጥፋት እንደሚቹሉ እስኪያሡ ድረስ አቅማቸውን ሊገነቡ ቻሉ፡፡

ከካህን እስከ ምእመን ድረስ ኃላፊነቱን ካልተወጣና በዝምታ ከተመለከትናቸው ይሄንን ሰይጣናዊ ዓላማ ከማሳካት እንደሚይመለሱ ላረጋግጥላቹህ እወዳለሁ፡፡ እዛው ያሉት እራሳቸውን ወንጌላዊያን ነን ሲሉ የሚጠሩ ከጳጳስነት እስከ ዲቁና ድረስ ያሉ ልጆቻቸውም የሚዘሩት ይሄንን መርዝ ነው፡፡

ልብ የሌላቸውና የሚያስተወሉ ናቸውና አያስተወሉም እንጅ ዘመኑ ደስ በሚያሰኙ ነገሮች እየተሞላ መማጣቱ ረሀብ፣ እርዛት፣ ጦርነት፣ ችጋር፣ ሰቆቃ ማብራከቱ ፍቅርና ሰላም መጥፋቱ የሚያስገነዝበን ዐቢይ ቁምነገር ቢኖር ጾም በዝቷል ይቀነስ፣ ጸሎት እረዝሟል ይጠር ወዘተረፈ. ብለን ሥጋችንን እንዲደላት በሚከብ ማስነፍን ሳይሆን ዓለም ስለተያዘችበት ጭንቅና ጥብ ሁሉ ምሕረት ይወርድ ዘንድ አጥብቀን የምናዝንበት የምንጾም የምንጸልይ የምንሰግድበት ዘመን መሆኑን በተረዳና ከሚሉት አሳሳች ምክር በታቀቡ ነበር፡፡

የሃይማኖት አባት ሐዋርያ የሆነ ሰው እንጹም፣ እንጸልይ፣ እንስገድ፣ ዓለምንና የዓለም የሆነውን ሁሉ አንወደድ እንጥላ፣ ትሕርምተኛ እንሁን ይላል እንጅ አንጹም አንጸልይ... ይላል እንዴ? ይሄ ምክር የአጋንንት እንጅ እንዴት ሆኖ ነው የመንፈስቅዱስ የሚሆነው?

ወንጌል የገባው ለወንጌል ቀናኢ የሆነ ማለት ራስን ጥሎ መስቀሉን ተሸክሞ ወንጌሉን ቃል በቃል ኖረውበት በሕይወታቸው ተርጉመው እንዳሳዩት እነኝሁ ዳንኪረኞች ካደረባቸው ክፉ መንፈስ የተነሣ እንደሚሉቿቸው ቅዱሳን ሥጋን ከክፉ መሻቱና ምኞቱ ጋር መስቀል እንጅ ለሥጋ ምቾትና ጥቅሞች ሚድር ሥጋዊ ጥቅምን ማሳደድ፣ ግላዊ ፍላጎትን ሃይማኖታዊ ገጽታ በማስያዝ ምንም በማያውቁ ምእመናን ላይ ጫና ማሳሳት ማለት አይደለም፡፡ "የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ" ገላ. 5፤24 "የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና" 1ኛ ጴጥ. 2፤21

እርግጠኛ ነኝ እነኝሁ አሳቾች ይሄንን አጥተውት አይደለም፡፡ ነገር ግን በሥጋ ፈቃድ ያበዱ፣ የተሸነፉ፣ ድል የተነሡ፣ የተንበረከኩ ከንቱ ግለሰቦች ስለሆኑ ሙሉ ለሙሉ የሚተከሩት ይሄንን ሥጋዊ ፈቃድ ፍላጎታቸውን ሚርካታቸው ላይ ነው እንጅ በዚህ ዕኩይ ግብራቸው እግዚአብሔር የሚቀየምና እነሱም የሚጎዱ መሆኑ ለቅጽበት እንኳን የሚያሳስባቸው በመሆኑ ነው የሚሠሩትን ስሕተት ሊያስተውሉ ያልቻሉት፡፡ "በመጨረሻው ዘመን እንደ ራሳቸው ምኞት የሚመላለሱ ዘባቾች በማዘበት እንደሚመጡ ይህን በፊት እወቁ፤" 2ኛ ጴጥ. 3፤3

እናም ምእመናን ሆይ! እረኞቻቹህን ለዩ እነማን እንደሆኑ እወቁ በተከላት እንዳትነጠቁ፡፡ ቀሚስና ቆብ ያጠለቀው ሁሉ እረኛ እንዳልሆነ ይህ ዘመን በሚገባ እያስረዳን እያስገነዘብት እያሳየን ነው፡፡ ሥጋዊ ፍላጎቱንና ምኞቱን ይዞ የገባው ወይም ለሥጋዊ ስሜቱና ፍላጎት የተንበረከከው ሁሉ ይንን ችግሩን ደዌውን በሽታውን በሌሎች የዋህን ላይ ለመጫን ለማጋባት ለማስተላለፍ የሚሯሯጠው ሁሉ አትጠራጠሩ የዲያብሎስ አገልጋይ ነው እንጅ በፍጹም በፍጹም የመድኃኒዓለም ክርስቶስ አገልጋይ አይደለምና ይሄንን የተከላ ቡድን በመከተል ወደ ጥልቁ የእሳት ባሕር እንዳትሰጥሙ በእጅጉ ተጠንቀቁ፡፡ ቤተክርስቲያንንም ከእነኝህ ተከላት አፅዱ፡፡ ይሄንን ሳታደርጉ እንቅልፍ አይወሰዳቹህ፡፡ በገዛ ደሙ ለዋጃት ቤተክርስቲያን ጥፋት ተጠያቂና ባለዕዳ እንዳንሆን፡፡

"የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምምያውነው። ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ፤ ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነውእንጂ በመብል አይደለም፤ በዚህ የሚሥሩባት አልተጠቀሙምና" ዕብ. 13፤7-9

**ለእነዚሁ ዳንኪረኞች ማስተላለፍ የምፈልገው መልእክት ቢኖር፡-** እንዲህ የምትሠሩትን እንዳታውቁ አድርጎ ደፍረት በተሞላበት እንቅስቃሴ ቤተክርስቲያንን እንድታውኩ የሚያደርጋቹህን ክፉ መንፈስ ድል ነስታቹህ ንስሐ በመግባት የሚጠብቅባቹህን ያህል መሆን ትችሉ ዘንድ ጾም ጸሎት ስግደት የተለየውን ዓለማዊ የአኗኗር ዘይቤያቹህን ትታቹህ እንደ ቅዱሳን እናት አባቶቻችን ሁሉ በብርታት ጾሙ ጸልዩ ስገዱ የተለያዩ ትሩፋትን በሚፈጸም ተጋደሉ፡፡ በማስመሰል ምሳሳቹህን ብቻ ክርስቲያን ሚድረጋቹህ ፍሬ እየሌለው ገለባ አድርጎ ያስቀራቹህል እንጅ አይጠቅማቹህም፡፡ "አይ! አንተን አይደለም ማንንም አንሰማም!" የምትሉ ከሆነም የጭፈራ መሣሪያቹህን ይዛቹህ ቢጤዎቻቹህን ሰብስባቹህ ወደ ጭፈራ ቤቶች ሔዳቹህ የጭፈራ ጥማቹህን እዚያ እንድትወጡ እየጠቆምን የእግዚአብሔርን ቤት ግን ከነበረ ማንነቷ ጋር ትተውልን ዘንድ በአጋእዝተ ዓለም ሥላሴ በመድኃኔዓለም ክርስቶስ ስም አጥብቀን እንለምናቹህለን!!

**ለተቀሩት ለደኅናዎቹ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላትና ለቅዱስ ፓትርያርኩ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሚቶሬዎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ማስተላለፍ የምፈልገው መልእክት ደግሞ፡ –** እርግጥ ነው አዎ ብዙ የቸገረ ነገር እናዳለ እናውቃለን፡፡ እነኝህ ከሀድያን ተኩላት እጅግ እንደበረቱባቹህና የቁም እስረኛ አድርገው ወልፍት እንዳትሉ አድርገው ፓስፖርት (የይለፍ ወረቀት) ሳይቀር ነጥቀው ከወዳጅ ዘመድ ሳይቀር እንዳትገናኙ አድርገው እንዳስቀመጧቹህና ማብደል ማፋታቹህን ለሕዝበ ክርስቲያኑ ከማገለጥ ይልቅ በለቅሶ በሱባኤያት ወደ እግዚአብሔር ማስሰብን ሚርጣቹህ ለዘመናት ይሄንን እያደረጋቹህ እንዳላቹህም እናውቃለን፡፡ ይህ ለቅሶ ጩኸታቹህ ከንቱ እንደሚይቀርም ተስፋ እናደርጋለን፡፡

ይሁንና በዚህ በተለመደው መንገድ ከመቀጠል ይልቅ አምላከ ቅዱሳንን ይዛቹህ እነኝህ ከሀዲያን ይሄንን የድፍረት ወሳኔያቸውን ነገ በእናንተ ስም በማጠቀም "ቅዱስ ሲኖዶስ ወሰነ" ብለው ከማወጃቸውና ይህ ሆኖ ቤተክርስቲያን ከባድ ፈተና ላይ ከመወደቋ እናንተም በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት ከማዋረዳቹህ ተጠያቂዎች ከማሆናቹህ በፊት እንደምንም የማናኛ ዘደውን ፈጥራቹህ ከምእመናንንና ደኅና ከሆኑት ካህናት ጋር በማሆን እንዲገቱ የሚዋርፉ ከሆነም በቀኖና ቤተክርስቲያን መሠረት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ታደርጉ ዘንድ ማስሰብ እወዳለሁ፡ "በገዛ ደመየዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።" የሐዋ. ሥራ 20፤28

**ለሕዝበ ክርስቲያኑ ማስተላለፍ የምፈልገው መልእክት ቢኖር፡ –** ሕዝበ ክርስቲያን ሆይ! የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በታሪኳ መናፍቃኑ እንደዚህ ዘመን የቤተክርስቲያንን ከፍተኛ አካል ቅዱስ ሲኖዶስን ጉልበት አቅም አሳጥተው ቀፍድደው ይዘው እንደፈለጉ የፋነኑበት ዘመን ኖሮ አያውቅም፡ ይህ ምን ማለት እንደሆነ በቅጡ የገባን አልመሰለኝም፡ ቤተክርስቲያን ተዋርዳለች ተደፍራለች፡፡ ይሔንን ፈተና ብዙዎቻችን የአንድ ሰሞን ወሬ ሆኖ እንደሚያልፍ አድርገን እያሰብን ነው፡ ይህ ግን እጅግ የተሳሳተ አደገኛ አማካከት ነው፡ ቅድስት ቤተክርስቲያን ከሌሎች ሀገራት የጠፉችውና በመናፍቃኑ የተወረሰችው አሁን እኛ እያሳየነው እንዳለነው ማዝናጋት ሁሉ በእነዚያ ሀገራት የነበረው ሕዝበ ክርስቲያን ባሳየው ማዝናጋትና ቸልተኝነት ቤተክርስቲያን ያጋጠማትን ፈተና በዝምታ በመሜልከታቸው ነበር፡፡

ብዙዎቻችን ነገሩን በቸልታ ከመሜልከት ከወሬና ከንፈር ከማምጠጥ ያለፈ እንደክርስቲያን ቤተክርስቲያንን ከአደጋ ለማጠበቅ ለማታደግ ካለብን ክርስቲያናዊ ኃላፊነትና ግዴታ አንጻር ምንም ያደረግነው ነገር የለም፡ ቅዱሳን ሐዋርያት ጻድቃን ሠማዕታት እናት አባቶቻችን እንደ ጎመን የተቀረደዱት እንደ ሽንኩርት የተላጡት በመንኮራኩር የተፈጩት እንደ ክርስቲያንነታቸው ቤተክርስቲያንን ለማጠበቅ የተጣለባቸውን ክርስቲያናዊ አደራና ዕዳ ለመወጣት ሲሉ እንጅ በአሰቃቂ አኳሃን የማሞት ሱስ ስለተጠናወታቸው አይደለም፡

ኧረ ባካቹህ እንንቃ! ቤተክርስቲያን እኮ ከባድ አደጋ ላይ ናት፡፡ ቅዱስ ሲኖዶስን አቅሚቢስ ሽባ አድርገውታል እኮ! እዚህ ሀገር ወስጥም የወያኔን ሹመኞች አስቀድሞ አባ ጳወሎስን አሁን ደግሞ አባ ማትያስን በማያዝ የቤተክርስቲያንን ስር እየቆረጡ ልምላሜዋን አድርቀውታል፤ መንጋዋን ወደ ተኩላት በረት አስኮብልለዋል፤ ቢገለጽ የሚያልቅ ጉዳትና ኪሳራ አድርሰውባታል፡፡ ይህ እዚህ ሀገር ወስጥም ሰሜን አሜሪካም የምናየው የመናፍቃኑ እንቅስቃሴ የተልእኳቸው የሚጨረሻ ምእራፍ ነው፡ ነባሩንና እውነተኛውን የቤተክርስቲያን አስተምህሮ ዶግማ ቀኖናና ሥርዓት ሽረው ኑፋቄና ክህደት የተሞላበትን የጥፋት ትምህርታቸውን "የቤተክርስቲያን ዶግማ ቀኖናና ሥርዓት ነው!" ብለው ለማወጅ የእንቅስቃሴያቸው መቅድም ነው፡

እናም ክርስቲያን ነኝ የምንልና ይህ ጥፋት እንዲደርስ የማንፈልግ ከሆነ ቤተክርስቲያንን ከጥፋት የማታደግ ዘመቻ ዛሬ ነገ ሳንል ማንንምና ምንንም ነገር ሳንፈራ ሚድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ይህንን ሚድረግ

ካልቻልን ግን አስማዮች እንጅ ክርስቲያኖች አይደለንምና ክርስቲያኖች ነን አንበል፡፡ ልዑል እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን ለማጠበቅ ከጥፋት ለማዳግ እንደክርስቲያን ከእኛ የሚጠበቅብንን ግዴታና ኃላፊነት እንደ እናት አባቶቻችን ሁሉ መወጣት እንችል ዘንድ ማታመኑን፣ ድፍረቱን፣ ጽናቱን፣ ቁርጠኝነቱን፣ ትጋቱን፣ ወኔ ወኔ፣ ብልሀቱን፣ ጥበቡን ሰጥቶን አደሎን ያንዣበበወን አደጋ እንድንከላ እንድናስወግድ አድርጎ ቤተክርስቲያንን ከጥፋት ይታደግልን ዘንድ ፈቃዱ ይሁንልን፡፡ አሜን!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com